## ዛሬም ነገም ኣገራችን ኦሮምያ፥ ህዝባችን ኦሮሞ፥ ኣላማችንም ነጻነት ነው!

በኦነግ የሚመራው የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ባለፉት ኣርባ ኣመታት ትግሉን ሊያጠፉ በፈረቃ የተሰለፉትን ጠንካራ የሚባሉ ጠላቶችን ሁሉ ካለምንም የውጭ እርዳታ በመቁዋቁዋም ካሁን ወዲያ ሊነቀል የማይችል ከብረት የጠነከረ ብሄረተኝነትም በህዝቡ ልብ ውስጥ ለመትከል ችሏል። የብሄርተኝነቱ መሰረትም ኦሮሞነትና የኦሮምያ ነጻነት ናፍቆት ነው። ዛሬ ኦሮሞውን *ኣንተ ኦሮሞ ነህ፥ ኣገርህም ኦሮምያ ናት* እያሉ የሚያስተምሩበት ዘመን ኣልፎኣል። በዚህ ተቃራኒም የባእድ ልሳን እየሆኑ ኦሮሞውን በመቅረብ *የለም ኣንተ ኢትዮጵያዊ ነህ፥ ኣገርህም ኢትዮጵያ ናት* እያሉ የነጻነት ትግሉን ለመቀልበስ የሚደረጉ ጥረቶች በተከታታይ ቢስተዋሉም የጥረቶቹ ኣላማ ተቀባይነትን ማግኘት ኣልቻለም። ዛሬም ወደፊትም ተቀባይነት ኣይኖረውም። ይህንን የማይናወጥ የብሄርተኝነት መሰረት በከፈሉት ውድ መስዋእትነቶች በህዝባችን ልብ ውስጥ ለተከሉት ሰማእታትና ዛሬም በያዙት ክቡር ኣላማ ጸንተው በትግሉ ላይ መስዋእትነቶችን በመክፈል ላይ ለሚገኙት ታጋዮቻችን የከበረ ምስጋና ይድረሳቸውና ዛሬ ኦሮሞ የብሄሩንና የሃገሩን ማንነት ከመረዳት ኣልፎ በፖለቲካ ህይወቱ ይሆነኛል ያለውን ለመወሰን ኣስፈላጊውን የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ብቃቱን ኣረጋግጦ ይገኛል። ይህ ደግሞ ለትግሉ ስኬታማነት ማረጋገጫ ሊሆን የሚችል ከሁሉም የላቀ መሰረታዊ ድል ሆኖ መታየት የሚችል ነው።

የኦሮሞ ብሄርተኝነት ከሁሉም ኣቅጣጫ የጎመራና ከቶ የማይቀለበስ ደረጃ ላይ መድረሱ ለህዝባችን ተስፋ ሰጪ የመሆኑን ያህል ለጠላት ደግሞ ኣሳሳቢ ሆኖ እየታየ ነው። በየዩኒቨርሲቲው፥ ኮሌጅና ትምህርት ቤቱ ሁሉ የሚታየው የኦሮሞ ተማሪዎች የኣንገዛም ባይነት ኣመጽ ለዚህ ኣንዱና ዋናው ኣብነት ነው። ዛሬ የቄቤ ትውልድ እየተባለ የሚታወቀው ወጣቱ ትውልድ በታላቆቹ ታጋዮች የተመዘገቡትን ድሎች ለመንከባከብና ቀሪዎቹን ድሎች ለመጎናጸፍ ከመላው ኦሮምያ ወቅቱ የሚጠይቀውን የትግል ቁርጠኝነት እያሳየ ይገኛል። የኦሮምያን ነጻነት የሚያረጋግጥ ብሄርተኝነት ተጠናክሮ መቀጠል ባለበት ሁኔታ ላይ ኣዲሱ ትውልድ ታሪክ የጣለበትን ሃላፊነት ለመወጣት ወደ ተግባር ገብቶ እንደሚገኝም ኢፉ ሆኗል። የትግሉ ጠላት ይህንን ፍትሃዊ ፖለቲካዊ ሂደት ለማጨናገፍ ከመጣር የተቆጠበበት ጊዜ የለውም። የተቻሉለትን የሃይልና የብልጣብልጥነት እርምጃዎችን ሁሉ በመውሰድ የኦሮሞን ብሄርተኝነት ለማኮላሸት ከመድከም ኣልቦዘነም። የሃይል እርምጃዎችን በመውሰድ የበርካታ ታጋዮችን ህይወት ኣጥፍቶኣል፥ ለኣካል ጉድለት ዳርጎኣል። ሺዎችን ኣስሯል፥ ሺዎችን ለስደት ህይወት ዳርጎኣል። በብልጣብልጥነት እርምጃዎቹም በርካታ ቁጥር ያላቸውን የኦሮሞ ብሄረተኞችን በኦነግ ከሚመራው የነጻነት ትግል ጎዳና ለማስወጣት ሲል ለፖለቲካ ኣላማው ማሳኪያ ብሎ በጠፈጠፈው ኦፒዲኦ ውስጥ በኣባልነት መዝግቦኣቸዋል። በነጻነት ትግሉ ጎራ ውስጥም በርካታ ተላላኪዎቹን ኣስርጎ በማስገባት ትግሉን ከውስጥ ለማፍረስ እንዲሰሩ ሲያሰማራ ቆይቷል። እነዚህ የሃይልም ሆነ የብልጣብልጥነት እርምጃዎች በሙሉ ግን የኦሮሞ ህዝብ ብሄረተኝነት ይበልጥ እንዲጠናከር ኣደረጉ እንጂ እንደታሰበው ትግሉን ኣጨናግፈው የታለሙለትን ግብ ኣልመቱም፥ ሊመቱም ኣይችሉም።

የወያኔ መንግስት በእጅጉ እያጋነነ የሚናገረው የባህል፥ የቁዋንቁዋና “ራስን በራስ የማስተዳደር” መብቶች ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ ሲያዩት ምን እንደሚመስል ከማንም በላይ የመናገር ሞራል ያለው በወያኔ የጭቆናና የጭካኔ በትር እየቆሰለ ያለው ህዝባችን ነው። “*ማን ይናገር የነበረ…*” እንዲሉ በስርኣቱ የተዘረጉት ፖለቲካዊ፥ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምን ያህል ስር የሰደዱ ስለመሆናቸው ራሱ የችግሩ ሰለባ የሆነው ህዝቡ እንዲናገር ሊፈቀድለት ይገባል። በኢትዮጵያ ኢምፓየራዊ ስርኣት ስር ለረጅም ዘመናት ሲማቅቅ የኖረው የኦሮሞ ህዝብ ለኢምፓየሪቷ ካበረከተው ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ኣኩዋያ ኣንድም ጊዜ

ያገኘው ክብርና ምስጋና የለም። ከትላንት እስከ ዛሬ በሃይል በተለጠፈበት ኢትዮጵያዊነት ሳቢያ ሞልቶ የፈሰሰ የሰቆቃ ህይወት ከማስተናገድ ውጭ ለኣንዲት ቀንም እንደ እውነተኛ ዜጋ ተቆጥሮ የፖለቲካ መብቱ ተጠቃሚ ሆኖ ውሎ ኣያውቅም። ትላንት ኢምፓየሪቷን የመሰረቱትም ሆነ ዛሬ ኢምፓየራዊ ስርኣቱን እንዳለ በመውረስ በቁጥጥራቸው ስር ያስገቡት የፖለቲካ ሃይሎች የኦሮሞን ህዝብ በቁጥር ብዙህነትና የኢኮኖሚ ጀርባ ኣጥንትነት እየመረራቸውም ቢሆን ለመቀበል ቢገደዱም ቅሉ ለዚህ ብዙሃንና ለኢትዮጵያ ህልውና ወሳኝ ለሆነ ህዝብ የሚገባውን የፖለቲካ መብቶች ሊመልሱለት ኣስበው ኣያውቁም።

ዛሬ ኦሮሞ ከትንሽ እስከ ትልቅ ማንነቱን ተረድቶ የኢትዮጵያ መንግስታትን የፖለቲካ ሻጥሮችና ደባ ከ ሀ እስከ ፐ በተገነዘበበት ወቅት በኦሮሞ ላይ ኢትዮጵያዊነትን ጭኖ ለማስቀጠል የሚያስብ ሃይል ካለ እሱ በቅድሚያ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር የሚተዋወቅም ኣይመስልም፣ ኣልያም ደግሞ እውነታዎችን ሁሉ እያወቀ ለግል ጥቅሙ ሲል በህዝቡ መብቶች ላይ ለመደራደር ራሱን ገበያ ያወጣ መሆን ኣለበት። ኣሁን ባለንበት ወቅት ለራሱ ህልውናና ጥቅም ሲል ከኦሮሞ ጋር ተደራድሮ *ትላንት ለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ፣ ካሁን ወዲያ ኣብረንህ እንድንኖር መልካም ፈቃድህን እንሻለን* ብሎ መጠየቅ የሚጠበቅበት የዘመናት ጭቆና ሰለባ የሆነው ህዝባችን ሳይሆን ጭቆናውን በጫንቃው ላይ የጫኑትና መቼም ቢሆን የማይሽር ቁስል ያቆሰሉት ወገኖች መሆን ኣለበት። ከኦሮሞ የሚጠበቀው ሃይሉን ኣስተባብሮ ጨቋኞች ያከናነቡትን የውርደት ሸማ ከላዩ ላይ ቀዶ መጣል እንጂ የውርደቱን ሸማ ያከናነቡትን ሃይሎች ተንበርክኮ መለማመጥ ኣይደለም።

ትላንት በስልጣን ላይ የነበሩትም ሆነ ዛሬ ስልጣን በእጃቸው ያስገቡት የኢትዮጵያ ገዢዎች በኦሮሞ ህዝብ ላይ በፍራቻ የተሞላ ንቀትና ጥላቻ እንደያዙ ኖረዋል። ዛሬም በዚሁ መቀጠላቸውን እየታዘብን ነው። ኦሮሞ ምንም በቁጥር ቢበዛ፣ ምንም ያህል ቢማር፣ ምንም ያህል የኢኮኖሚ ጀርባ ኣጥንት ቢሆን ከቁጥጥራችን ውጭ መውጣት ኣይችልም ብለው ራሳቸውን ኣሳምነዋል። የህዝቡን ነጻነትና የኦሮምያን ሉኣላዊነት ማስመለስን ኣላማው ያደረገው ትግሉም እነሱ ዘንድ ሁሌም "ህልም" ነው። ይህ ደግሞ የሁሉም ጨቋኛኝ ሃይሎች ባህሪይ ነው። በሃይል እስከሚገደዱ ድረስ በመዳፋቸው ስር ላለው ህዝብ የመብት ጥያቄዎች እውቅና ኣይሰጡም። ታላቁ የህንድ ታጋይ ማህትማ ጋንዲ ይህንን የጨቋኞች ባህሪይ በኣጭርና ግልጽ ቁዋንቁዋ ገልጾታል። "*First they ignore you, then they laugh at you, then they fight you, then you win.* (*መጀመሪያ ላይ ጆሮ ዳባ ይሉሃል፣ ከዚያም ይስቁብሃል፣ ከዚያም ይዋጉሃል፣ ከዚያም ታሸንፋቸዋለህ።*)" ከዚህ እውነታ መረዳት የሚቻለው ጠላት ሁሌም ቢሆን በልምምጥ የማይሸነፍ መሆኑን ነው። ልምምጥ ቀርቶ በቁርጠኝነት እየታገሉትም ቢሆን የትግሉ ክንድ ተጠናክሮ ጫና እስካላሳረፈበት ድረስ ንቀቱን የሚቀጥል ስለመሆኑ የጋንዲ መልእክትም ያስገነዝባል። ጠላት የራስን ማንነት ትቶ የሱን ማንነት በውሰት ቢቀበሉለት ሆድ ብሶት ርህራሄ ኣያሳይም። ራስን ሸጦ እሱን መምሰል ለባሰ ንቀት ከመጋበዝ ውጭ እንደ ግልም ሆነ እንደ ህዝብ ክብርን ኣያጎናጽፍም። በራስ ማንነትና የትግል ኣላማ ጸንቶ በሁሉም መንገድ ወጥሮ በመያዝ መፈናፈኛ ካላሳጡት ጠላት የሰውን ልክ ማወቅ ኣይችልም።

ዛሬም በዚህ ክፍለ ዘመን ራሳቸውን እያታለሉ የኦሮሞን ህዝብም ለማታለል የሚፈልጉ ኣንዳንድ የፖለቲካ ሃይሎች ትላንት ራሳቸው ሳይቀር ሲያስተምሩ ከኖሩት ታሪክ መማር እንዴት እንዳቃታቸው ግልጽ ኣይደለም። የኦሮሞ ህዝብ ብሄርተኝነት የት ደረጃ ላይ እንደደረሰ እያዩ ኣይናቸውን መጨፈን መሞከራቸው ኣስገራሚ ነው። ዛሬ ይቅርና ትላንት በጭለማው ዘመንም ቢሆን እንዲህ ያሉት መሰል ጥረቶች ኦሮሞን ኣታልለው በኦነግ ከሚመራው የትግል ጎዳና ሊያስወጣው ኣልቻሉም። ኦነግ ገና ተወልዶ ዳዴ እያለ ሳለም መሰል ተግዳሮቶች ውስጥ ነበር ራሱን ያገኘው። ይሁንና እነዚያን ተግዳሮቶች በሙሉ

በድል በመወጣት በሂደት እየጎለበተ እነሆ ዛሬ ደረሰ። ዛሬም ይህ ተግዳሮት አልተለየውም። ይሁን እንጂ ድሮና ዘንድሮ አንድ አይደሉም። ኦነግ ትላንት በአንድ እጁ ኦሮሞውን ኦሮሞ ነህ፣ አገርህም ኦሮምያ ነው እያለ ሲያስተምር በሌላ እጁ ደግሞ ዘርፈ ብዙ ጠላቶቹን ሲፋለም ኖሯል። ዛሬ ግን ቢያንስ ኦሮሞውን ስለ ኦሮሞነቱ በማስተማሩ ስራ ስኬት ተመዝግቧልና ካሁን ወዲያ የሚቀረው መንገድ እንደቀደመው አይነት ፈታኝ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ከሁሉም ነገር በላይ የትግሉ ባለቤት የሆነው የኦሮሞ ህዝብ ነቅቶ ከመሪ ድርጅቱ ጎን ቆሟልና ትግሉን የሚያጨናግፉ እንቅስቃሴዎችን በዝምታ አይመለከትም። ትግሉ የራሱ ትግል መሆኑን ስለተገነዘበ እሱ ራሱ ይታገላል። ይህም ባለፉት 20 አመታት ውስጥ ተመላልሶ የታየ ሃቅ ነው።

የኦሮሞ ህዝብ ዛሬ ባለንበት ዘመን ከውጭም ሆነ ከትግሉ ጎራ ውስጥ ተሳስተው ህዝቡን ለማሳሳት ከሚሞክሩት የፖለቲካ ሃይሎች የሚመጡትን የእኔ-አውቅልሃለሁ ፖለቲካ ቅጽበታዊ ምላሽ መስጠት እንደሚችል የሚመሰክሩ ምሳሌዎች ብዙ ናቸው። እንደ አንድ ዋና ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በ2012 መጀመሪያ ላይ የተከሰተውን ሁኔታ ማስታወስ ይቻላል። በተጠቀሰው ወቅት አንድ ራሱን ከኦነግ ያገለለ ቡድን ራሱን ኦነግ ብሎ በመጥራት "በአዲስ አመት አዲስ ራእይ ሰንቀናል። ከዛሬው እለት ጀምሮ የኦነግን የፖለቲካ ፕሮግራም ቀይረናል፣ ካሁን በሁዋላ የኦነግ አላማ ኢትዮጵያዊነት እንጂ ኦሮምያዊነት አይደለም" በማለት አወጀ። አሉ በሚባሉት አማርኛ ተናጋሪ ተቃዋሚ ድርጅቶች ዘንድ እጅግ ብዙ ተጨበጨበለት። ቡድኑ የኦነግን ውድቀት ለማየት የሚመኙ ወገኖችን በሙሉ በደስታ ከማስፈንደቅ አልፎ የልብ ልብ ተሰምቶአቸው የኦነግን አላማ ለማጨናገፍ ከጣሪያ በላይ እየጮሁ እንዲፎክሩ እንዳበረታታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነበር። የአማርኛ ፕሮግራም የሚያሰራጩ የተቃዋሚዎችም ሆነ አንዳንድ አለም አቀፍ ሚድያዎች ለቡድኑ ልቅ የሆነ የአየር ጊዜ እየሰጡት ራሱን በሚገባ እንዲያስተዋውቅበት በመጋበዝ አበረታቱት። ይሁን እንጂ ታዲያ በዚህ ወቅት በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የነበረው ድባብ ተቃራኒው ነበር። በዚህ አስነዋሪ መልኩ የኦነግን የፖለቲካ ፕሮግራም ቀይሬያለሁ ሲል ለተሰማው ቡድን የኦሮሞ ህዝብ አፋጣኝና ወሳኝ የሆነ ምላሽ ሰጠ። በዚህ መልኩ ነበር ያ ቡድን ከኦሮሞ ህዝብ የፖለቲካ ባህር የተተፋው። መጨረሻው የታሪክ አተላ ሆኖ መቅረት ሆነ። ቡድኑን እያደፋፈረ ለዚህ ውድቀት የዳረገው ጠላትም ሽንፈቱን አብሮት ተከናነበ። አሁን ሁሉም ነገር ዝም ሆኗል። ቄሱም ዝም መጽሃፉም ዝም!

ህሊና ያለው ግለሰብም ሆነ ቡድን ከዚህ የታሪክ ክስተት ብዙ ሊማር ይችላል። ኦሮሞ ምን እንደሚፈልግ ከዚህ እውነታ በመነሳት በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ኦሮሞ የሚፈልገው በአላማው ጸንቶ የተጠናከረ ክንዱን በጠላት ላይ የሚሰነዝር ኦነግን ማየት እንጂ ከድርጅቱ እየተለዩ በመሄድ ለሌላ ወገን የፖለቲካ አላማ ማበረታቻ ተብለው የተጻፉና የተቀመሩ መዝሙሮችን አብሮ መዘመርን አይደለም። የኦሮሞ ህዝብ ብሄረተኝነት ከምን ጊዜውም በላይ ተጠናክሮ አይበገሬነቱን ማረጋገጡ ተሰፋ ያስቆረጣቸውን ወገኖች እየቀረቡ *ኣይዙኣችሁ፣ ኦሮምያዊነትን ጥለን ኢትዮጵያዊነትን ተቀብለናል* የሚል መልእክት ያዘለ ተንበርካኪነት የኦሮሞ ህዝብን ፍላጎት አይወክልም። እንዲህ ያለው አቀራረብ በራሱ ህሊና የሚያስበውን ብሄረተኛ የኦሮሞ ህዝብ ቀርቶ በኦፒዲኦ-ወያኔ ማእቀፍ ውስጥ ላሉት የኦሮሞ ልጆችም የሚዋጥ አይደለም። ለይስሙላም ቢሆን በአንቀጽ 39 ስር የተቀመጠው የወያኔ ህገመንግስት ራሱ ብሄር ብሄረሰቦች በሂደት አንድ ቀን አብሮ መኖሩ ካላዋጣቸው ተለያይተው የየራሳቸው መንግስት መመስረት እንደሚችሉ በመጠቆሙ ለኦሮሞ ህዝብ የኢትዮጵያዊነትን አማራጭ ብቻ ከሚያቀርቡለት የፖለቲካ ሃይሎች በተሻለ መልኩ ቅርበት ያለው ነው ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም።

በ1976 ኣም የወጣው የኦነግ የፖለቲካ ፕሮግራም እነ ኀበና ዳጩን በከሃዲነት ኣስቀምጧል። ኀበና ከሃዲ ተብሎ የተቀመጠው ያለ ኦሮሞ ህዝብ ፈቃድ ለምኒልክ ወግኖ የኦሮሞን ሃገር ሉኣላዊነት በሃይል በማስደፈሩ እንደነበር ኣይካድም። በወቅቱ የፖለቲካ ፕሮግራሙን የነደፉትና ዛሬ ከኦነግ የተለዩ ግለሰቦችም በዚህ ያምኑ እንደነበር ይታሰባል። በወታደራዊ ጀግንነቱ ካልሆነ በስተቀር ምንም ኣይነት የፖለቲከኛነት ንቃት ያልነበረውን ኀበና ከሃዲ ካልነው ዛሬ ባለንበት የሰለጠነ ዘመን የፖለቲካ ንቃቱ እያላቸው የኦሮሞን ህዝብ ጥቅም ጎድቶ የሌሎችን ፍላጎት የሚያሟላ ኣስተሳሰብ የሚከተሉስ ምን ሊባሉ ይሆን?

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ዛሬም ሆነ ነገ ኣገራችን ኦሮምያ፣ ህዝባችን ኦሮሞ፣ ኣላማችንም ነጻነት ነው ብሎ ያምናል። በኣላማ ከሚመሳሰሉትና ለእውነተኛ ደሞክራሲና የራስን እድል በራስ በመወሰን መብት ከሚያምኑት ሃይሎች ጋር የትግል ኣጋርነት መስርቶ ሲታገል ቆይቷል፣ ኣሁንም በኣጋርነት ይታገላል። ኣላማውን ከማይቀበሉለትና በምንም መልኩ ተቻችሎ ኣብሮ ለመስራት ኣስቸጋሪ ከሆኑ ሃይሎች ጋር ለመሞዳሞድ የሚደረግን የተንበርካኪነት እንቅስቃሴ ግን ኣሳፋሪ መሆኑን ይገነዘባል። ኣብዛኛውን የእድሜያቸውን ዘመን ለኦሮምያ ነጻነት ሲታገሉ ኖረው በስተመጨረሻ ላይ ኦሮምያን ወደ ጎን ብለው ለኦሮሞ ህዝብ መብት መከበር እውቅና ለነገፈገችው ኢትዮጵያ ህልውና ቅድሚያ መስጠት ኣስነዋሪ ክስተት መሆኑን ልናሰምርበት እንወዳለን። ኦነግ የሌሎችን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል የኦሮሞን ህዝብ ፍትሃዊ መብት ቆርሶ ለመስጠት የሚያስገድደው ሁኔታ የለም። የሌሎችን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል የኦሮሞን ህዝብ የፖለቲካ መብቶች መሸራረፍ ኣስፈላጊ ሆኖ ሊቀርብ ኣይችልም። ምክንያቱም ለኦሮሞ ህዝብ መብት መከበር ትግል በሚካሄድበት ተመሳሳይ ወቅት የሌሎችንም ህዝቦች መብት ለማረጋገጥ መታገል እንደሚቻል ግልጽ ነውና። ስለሆነም የተጎራባቾችን የጋራ ቤት ለመገንባት ሲባል የራስን ቤተሰብ መኖሪያ ቤት ማፍረስን ኦነግ ይቃወማል። የኦሮሞን ህዝብ ነጻነትና የኦሮምያን ሉኣላዊነት ለማረጋገጥ ትላንት የተጀመረው ትግል ዛሬም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ደግመን ደጋግመን ማስገንዘብ እንወዳለን። የኦሮሞም ህዝብ ለድርጅቱና ለፍትሃዊ ትግሉ እንደተለመደው ሁሉ ዋርዲያ በመቆም ትግሉን ያፋፋማል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ

መጋቢት 31, 2013